የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፳፱
አዲስ አበባ የካቲት ፰ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 29
ADDIS ABABA 15th February, 2013

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፯፻፹፭/፪ሺ፭ ዓ.ም

ለኢትዮጵያ-ኬንያ ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ...........................................ገጽ ፮ሺ፰፻፳፰

CONTENTS

Proclamation No. 785/2013

African Development Fund Loan Agreement for Financing Ethiopia-Kenya Electricity Highway Project Ratification Proclamation .............................................. Page 6828

## አዋጅ ቁጥር ፯፻፹፭/፪ሺ፭

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለኢትዮጵያ- ኬንያ ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፩፻፶ ሚሊዮን ዩ.ኤ (አንድ መቶ ሃምሣ ሚሊዮን ዩኒትስ ኦፍ አካውንት) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ ዲሴምበር ፭ ቀን ፪ሺ፲፪ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፴ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION No. 785/2013

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AFRICAN DEVELOPMENT FUND

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund stipulating that the African Development Fund provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of 150,000,000 U.A (one hundred fifty million Units of Account) for financing Ethiopia-Kenya Electricity Highway Project was signed in Addis Ababa on the 5th day of December, 2012;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 7th day of February, 2013;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

| ያንዱ ዋጋ Unit Price | 2.30 |
|---|---|

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለኢትዮጵያ-ኬንያ ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፹፭/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

፪. **የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.አ.አ. ዲሴምበር ፭ ቀን ፪ሺ፲፪ በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 2100150027844 በዚህ አዋጅ ፀድቋል::

፫. **የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፩፻፶ ሚሊዮን ዩ.ኤ. (አንድ መቶ ሃምሣ ሚሊዮን ዩኒትስ ኦፍ አካውንት) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል::

፬. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ የካቲት ፰ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "African Development Fund Loan Agreement for Financing Ethiopia-Kenya Electricity Highway Project Ratification Proclamation No. 785/2013".

2. **Ratification of the Agreement**

The Loan Agreement Number 2100150027844 signed in Addis Ababa on the 5th day of December, 2012 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund is hereby ratified.

3. **Power of the Ministry of Finance and Economic Development**

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of 150,000,000 U.A (one hundred fifty million Units of Account) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. **Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 15th day of February, 2013.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL**

**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**